# ወርቅ ላበደረ ጠጠር

ወያኔ የሚባል ፡ ከትግሬ የመጣ
ይለምን የነበር ፡ ያጣ የገረጣ
ወንድም አይሉት ፡ ጠላት ፡ የሐገር ባላንጣ
እንደ ቁርስ ምሳው ፡ የደረቀ ቂጣ
አገሬን ሸንሽኖ ፡ ይጣጣላል እጣ
ማን አለብኝ ብሎ ፡ ዛሬስ አይን አወጣ
ላገር ተቆርቋሪ ፡ ጠፋና እሚቆጣ
ይዘልብን ጀመር ፡ ወግድ የሚል ቢያጣ ::

ያጋጣሚ ነገር ፡ ሹምባሽ ዛሬ ገኖ
አንበሳ አንቀላፍቶ ፡ ዝንብ ባለቀን ሆኖ
እንዳምባሻ ቂጣ ፡ ቆራርሶ ሸንሽኖ
አገር ሲያፈራርስ ፡ እንዳሻው በትኖ
ሞቱ ላይቀርለት ፡ በፍርሀት ታፍኖ
በነ ሥም አይጠሬ ፡ እያለቀሰ አዝኖ
ሰው እንዴት ይሞታል ፡ እንደፍየል ቀዝኖ ::

አይ የጊዜ ነገር ፡ አያመጣው የለ
ድህነት ሲቆላው ፡ እየተቀበለ
ቤት ለእንግዳ ብሎ ፡ ችሎ እንዳላዘለ
አብልቶ አጠጥቶ ፡ እንዳልተካፈለ
እጁን ተነከሰ ፡ ውለታ በዋለ
ጠኔው ታግሶለት ፡ በተደላደለ
ትናንት ተረሳና ፡ ትዕቢቱ አየለ
ጊዜ ዘንበል ብሎ ፡ ስላቆለቆለ
ከየት እንደመጣ ፡ የት እንደበቀለ
በጥጋብ ተጋርዶ ፡ መቼ ተስተዋለ
ወገን ካደገበት ፡ እየተነቀለ
ወርቅ ላበደረው ፡ በጠጠር ከፈለ
ለችግሩ ደርሶ ፡ አይዞህ እንዳላለ ::

ፋሽስትን በታሪክ ፡ ካለን ተመክሮ
ጸረ ሕዝብ ቢሆንም ፡ ግብሩ በተፈጥሮ
ገዳይና አሳዳጅ ፡ የሚያሰቃይ አስሮ
አይሸጥም አገሩን ፡ እንደእቃ ቸርችሮ
አጥር አያፈርስም ፡ ለባዕድ ተቀጥሮ
እንኳን አገር ሊሸጥ ፡ ዳሩን አስከብሮ
ጎረቤቱን ሁሉ ፡ በጭንቅ አሸብሮ
ግዛቱን ያስፋፋል ፡ ድንበሩን ተሻግሮ ::

የኛ ግን ፋሽስቱ ፡ አገራችን ያለው
የሸነሸነ ፡ አገር የሚቸረው
አንገት ቆርጦ አልቆመ ፡ ከጎኑ ጀመረው
ጣሊያን አይሉት ድርቡሽ ፡ ጭራሽ መላም የለው
እሱ ያልሆነውን ፡ እኛ ሁን እያልነው
ወንሜ ነህ እያልን ፡ መከራ አሳየነው
ተከባብሮ መኖር ፡ መች እግዜር አደለው ።

ከወራሪ ጠላት ፡ መች ተናንሶ አመሉ
የወያኔ ትግሬን ፡ ወንድም አትበሉ
ያገሬን ገበሬ ፡ አርገው ከመሃሉ
ወያኔና ድርቡሽ ፡ ወገኔን ሲቆሉ
ማን እንዳይከፋ ፡ ማን እንዳይቆጣ ፡ ደርሶ ማባበሉ?
ገሸሽ ማለት ነው ፡ ካስፈራችሁ ትግሉ
በወንድማማች ሥም ፡ ይብቃ መደለሉ
ኢትዮጵያ እስክትጠፋ ፡ ታገሱ የምትሉ ።

ማነው ያገር ወዳጅ ፡ ማነው ወገንተኛ
ለደሀው አሳቢ ፡ የእውነቱ ዳኛ
አገሩ ተወስዶ ፡ እንቅልፍ የሚተኛ
ወያኔ ካልሆነ ፡ የትግሬ ምንደኛ
ደሀ ሆኖ ማደግ ፡ ያረገው ቂመኛ
ወገኑን በበቀል ፡ የሚሸጥ ቅጥረኛ
እግዜር የሰጠውን ፡ በልቶ የማይተኛ
ቅና ብሎ ፈጥሮት ፡ ምቀኛ ቁራኛ
ያርባ ቀን እድሉን ፡ ያመካኛል በኛ
ለምኖ አዳሪ ፡ አጎብዳጅ ጥገኛ
ድንበር ሳይከበር ፡ እንቅልፍ የለን እኛ
ትንሹም ትልቁም ፡ ዝመት በጎጠኛ ።

ሸፍት በከሃዲው ፡ አምጽ በወያኔ
እንደለመደበት ፡ ይግባና መድህኔ
ቢያሻው ፉል ይቀቅል ፡ ይባሸር በጂኔ
ያረብ ተላላኪ ፡ ወያላ አረመኔ
ጥጋቡን አልቻለም ፡ ይፈተን በጠኔ
እሹሩሩ ሲባል ፡ ዛሬስ መጣ ባይኔ
እሱን ለማባበል ፡ ትዕግስቴ አልቋል እኔ ።

ታዛቢው